## የጊዜው ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ።

# የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ ያላቸው ፡ መብት ።

ዊልያም ፡ ኤች ፡ ዩዊንግ ።*

## መግቢያ ።

የ፲፱፻፹፯ ፡ ዓመት ፡ ምሕረቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፵፪ ፡ "ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ ለመኖር ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ የሥራ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋምና ፡ በማናቸውም ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ አለው ።"[1] ይላል ። የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋምም ፡ ሆነ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ለመሆን ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ ሕጉ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚወስነው ፡ የማወቁ ፡ ጉዳይ ፡ ከጊዜው ፡ አሳሳቢ ፡ ጥያቄዎች ፡ አንደኛው ፡ ነው ።

የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ትእዛዝ ፡ እንደተሻሻለ ፡ እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ትእዛዝ ፡ ሥር ፡ የወጣው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ[2] ፡ "የመንግሥት ፡ ሠራተኞች"፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ማንኛውንም ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የቀጠረውን[3] ፡ ሰው ፡ የሚያጠቃልል ፡ መሆኑን ፡ ሲገልጽ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ኰሚሽነሮች ፡ የሚኒስቴሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሚያጸድቀው ፡ መሠረት ፡ አንዳንድ ፡ ሠራተኞችን ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ተጠቃለው ፡ እንዳይጠሩ ፡ ሊያደ

---

* በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መምህር ። በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ሃላፊ ፡ የሆኑት ፡ ዶክተር ፡ ሥዩም ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔርና ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪ ፡ የሆነው ፡ አማኑኤል ፡ ነጋሣ ፡ የዚህን ፡ ጽሑፍ ፡ ረቂቅ ፡ ተመልክተው ፡ ተቃዋሚ ፡ አስተያየቶችን ፡ ስለሰጡኝ ፡ ምስጋናዬ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

1. በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠው ፡ አንቀጽ ፡ ፵፪ ፡ የአማርኛው ፡ ቅጂ ፡ አዲስ ፡ ትርጉም ፡ ነው ። ተተርጉሞ ፡ የሚገኘው ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቅጂ ፡ "ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ ለመተዳደር ፡ መብት ፡ አለው ፤ ለዚሁም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ማኅበሮችን ፡ ለማቋቋምና ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ፡ " ይላል ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፻፳፭ ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ መደበኛ ፡ (ኦፊሲየል) ፡ ቋንቋ ፡ አማርኛ ፡ ነው ፡" ስለሚል ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀምነው ፡ በይበልጥ ፡ ትክክል ፡ በሆነው ፡ በአማርኛው ፡ ቅጂ ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ ልዩነት ፡ በማመልከትና ፡ አዲሱን ፡ ትርጉም ፡ በመለገስ ፡ ረገድ ፡ የረዱት ፡ አቶ ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፤ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መምህር ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።
2. ትእዛዝ ፡ ቁ፡ ፳፫ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፫ ፤ የ፲፱፻፷፬ቱ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ትእዛዝ ፡ እንደተሻሻለ ፤ ትእዛዝ ፡ ቁ. ፳፰ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፺ ፡ (ትእዛዝ ፡ ቁ. ፳፫ ፡ በትእዛዝ ፡ ቁ. ፳፰ ፡ እንደ ተሻሻለ ፤ ከንግዲህ ፡ "ትእዛዝ ፡" ተብሎ ፡ የሚጠራው) ፡ እና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ቁ . ፩ ፤ ፲፱፻፶፬ ፤ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁ. ፪፻፱ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፺ ፤ (ከንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ "የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡" ተብሎ ፡ የሚጠራው ።)
3. የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ተብለው ፡ ቢጠሩም ፡ የጦር ፡ ኃይሎች ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊትና ፡ ዳኞች ፡ በትእዛዙና ፡ በሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስር ፡ አይጠቃለሉም ። ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፪ ፡ ቍ. የተጠቀሰው ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፤ የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁ. ፫ ።

ርጉ ፡ መቻላቸውን ፡ ያስረዳል ።[4] ይሁንና ፡ ይህንን ፡ ጭብጥ ፡ ለመመርመር ፡ ይረዳን፡ ዘንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ መካከል ፡ የሚፈጥራቸውን ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ለየብቻቸው ፡ መመልከት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ክፍሎች ፡ (፩) ፡ መደበኛውን ፡ የመንግሥቱን ፡ የማስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የተቀጠሩ ፡ ሠራተኞችና ፡ (፪) ፡ "መንግሥት ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ ወይም ፡ የቴክኒክ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በሚያስተዳድሯቸው ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ንግድ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ለትርፍ ፡ በሚሠሩ ፡ ሌሎች ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ ተቀጥረው ፡ የሚሠሩ ፡"[5] ሠራተኞች ፡ ናቸው ።

ሀ/ <u>በመንግሥት ፡ እየተመሩ ፡ ለትርፍ ፡ በሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ ሠራተኞች</u> ፤

ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ለተመደቡ ፡ በአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ላልሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር፡ የማቋቋምንና ፡ በኅብረት ፡ ክርክር ፡ የመጠቀምን ፡ መብት ፡ በግልጽ ፡ ይሰጣቸዋል ።[6] እነዚህ ፡ አናቅጽት ፡ አግባብ ፡ ሊኖራቸው ፡ የሚገባው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ኰሚሽነር ፡ በትእዛዙና ፡ በሕግ ፡ ማስታወቂያው ፡ ሥር ፡ አይጠቃለሉም ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ ለሚያወጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ሠራተኞች ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ቀርቧል ።[7] ይህንን ፡ አቅዋም ፡ ለመደገፍ ፡ ሁለት ፡ የቀረቡ ፡ ወይም ፡ ሊቀርቡ ፡ የሚችሉ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። አንደኛ ፡ አዋጁን ፡ ያረቀቁት ፡ ሰዎች ፡ በአዋጁ ፡ ውስጥ ፡ "ሠራተኞች" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ይህን ፡ ጠባብ ፡ መስክ ፡ እንዲሸፍን ፡ አስበው ፡ ነበር ፡ ወይም ፤ ይኸው ፡ ቃል ፡ በሚተረጐምበት ፡ ጊዜ ፡ በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ በሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገትና ፡ ማኅበራዊ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ መካከል ፡ የሥልጣን ፡ መደራረብ ፡ እንዳይፈጠር ፡ ይኸው ፡ ጠበብ ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ እንዲሰጠው ፡ አስበው ፡ ነበር ፤ ለማለት ፡ ይቻላል ። የአዋጁ ፡ አጻጻፍ ፡ እንደዚህ ፡ ላለው ፡ ውሳኔ ፡ ፍንጭ ፡ ስለማይሰጥ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ እንዳንከራከር ፡ ችግር ፡ ይፈጥርብናል ። የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደርያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሳይፈጠር ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ በረቀቀው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ በአዋጁ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የአጻጻፍ ፡ መመሳሰል ፡ የአዋጁ ፡ አርቃቂዎች ፡ አዋጁን ፡ ባረቀቁበት ፡ ጊዜ ፡ በሃሳባቸው ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔ

---

4. ከዚያው ።
5. ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፷፯ ፤ ቁ፡ ፪(ረ) (፬) ፤ አዋጅ ፡ ቁ፡ ፷፬ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፴፫ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁ፡ ፲፩ ፡ (ከንግዲህ ፡ 'አዋጅ ፡' ተብሎ ፡ የሚጠራው) ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ትንሽ ፡ ለወጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። እሱም ፡ "በልዩ ፡ ሕጎች ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔዎች ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡" የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ "ከእንዳስትሪያል ፡ ወይም ፡ ከንግድ ፡ ሥራ ፡ ማካሄጃዎች ፡ ጋር ፡ በመንግሥት ፡ ወይም ፡ በአስተዳደር ፡ ወይም ፡ በቴክኒክ ፡ ክፍሎች ፡ መሪነት ፡ በሚደረጉ ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ፡" ይላል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ፡ ፪ሺ፭፻፲፪(፪) ። ያሁኑ ፡ ሐተታ ፡ በአዋጁና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጥቂት ፡ የአጻጻፍ ፡ ልዩነት ፡ በሕጉ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ መካከል ፡ የሚያስከትለውን ፡ ልዩነት ፡ ወይም ፡ የያንዳንዱን ፡ ሐረግ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ የሚመለከት ፡ አይደለም ።
6. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፪(ረ) ፤ ፳(ሀ) ፤ ፳፫ ።
7. በይልማ ፡ ኃይሉ ፡ የተጻፈውን ፤ ስለ ፡ <u>አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ በ፲፱፻፷፯ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ የተጠበቁና ፡ በሥሩ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ሠራተኞች</u> ፤ ተመልከት ፡ (፲፱፻፸ ፤ ያልታተመ ፤ በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ )፡ ገጽ ፡ ፳፫ - ፳፬ ።

ሩ ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ትእዛዝ ፡ እንዳልነበረ ፡ ያሳያል ። በአዋጁም ፡ ሆነ ፡ በትእዛዙ ፡ ውስጥ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ኰሚሺነሮች ፡ በአዋጁ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ ለየትኞቹ ፡ ሠራተኞች ፡ እንደሆነ ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ የሚያሳይ ፡ ነገር ፡ የለም ። እንዲያውም ፡ የኰሚሽነሮቹ ፡ ሥልጣን ፡ የትኞቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በትእዛዙና ፡ በሕግ ፡ ማስታወቂያው ፡ ሥር ፡ እንደሚመጡ ፡ መወሰን ፡ ነው ። የሥልጣን ፡ መደራረብ ፡ ጉዳይ ፡ ችግር ፡ የሚያስከትል ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ኰሚሽነሮቹ ፡ በመንግሥት ፡ እየተመሩ ፡ ለትርፍ ፡ በሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩትን ፡ (non-managerial) ሠራተኞች ፡ ከትእዛዙና ፡ ከሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሥር ፡ እንዳይቆጠሩ ፡ በመወሰን ፡ መፍትሔ ፡ ሊያገኙ ፡ ይችላሉ ።

ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ ሁለተኛው ፡ ክርክር ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ ትእዛዙ ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይሉን ፡ ያገኘው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፷፯ ፡ ስለሆነ ፡ ትእዛዙና ፡ በሥሩ ፡ የወጣው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ከአዋጁ ፡ ጋር ፡ በሚጻረሩበት ፡ ጊዜ ፡ አዋጁ ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ አይገባም ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፷፯ም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

"ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ የሚኒስትሮቹን ፡ ሁሉ ፡ የሥራ ፡ አኳኋን ፡ አቋቁሞ ፡ ይወስናል ። የመሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይሾማል ፡ በማዕርግ ፡ ያሳድጋል ፡ ያዛውራል ፡ ከሥራ ፡ ያግዳል ፡ ይሽራልም ።"

አዋጁ ፡ ለማንኛቸውም ፡ ዓይነት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ አግባብ ፡ የለውም ፡ ብለው ፡ የሚከራከሩ ፡ ሰዎች ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችን ፡ አስተዳደርና ፡ አቀጣጠር ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ቁጥር ፡ መሠረት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተሰጡ ፡ ስለሆነ ፡ እነሱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ በአዋጅ ፡ ሊተዳደሩ ፡ አይችሉም ፡ ብለው ፡ ይከራከራሉ ።[8]

ይህ ፡ ክርክር ፡ በአሁኑ ፡ ጭብጥ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አግባብ ፡ ትክክለኛ ፡ መስመር ፡ የያዘ ፡ አይደለም ። አዋጅ ፡ በማወጅ ፡ ረገድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሚያከናውኑት ፡ ተግባር ፡ አላቸው ። ማንኛውም ፡ አዋጅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ካላጸደቀው ፡ በስተቀር ፡ ሕግ ፡ አይሆንም ። የአሠሪና ፡ ሠራተኛን ፡ ጉዳይ ፡

8. የትእዛዙ ፡ መግቢያ ፡ በተጨማሪ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ. ፷፯ን ፡ ይጠቅሳል ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ. ፷፯ እንዲህ ፡ ይላል ።
"የቀሩት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሹመት ፡ የሚያገኙበት ፡ በማዕረግ ፡ የሚያድጉበት ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ የሚዛወሩበት ፡ ከሥራ ፡ የሚታገዱበት ፡ ሥራ ፡ የሚለቁበትና ፡ የሚሰናበቱበት ፡ ሁኔታና ፡ የአስተዳደሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሚያወጣውና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወዶ ፡ ተስማምቶበት ፡ ወዶ ፡ በሚያውጀው ፡ ደምብ ፡ መሠረት ፡ ይካሄዳል ።"
በተለይም ፡ በትእዛዙ ፡ መግቢያ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሶ ፡ ስለሚገኝ ፡ ይህ ፡ ቁጥር ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ መስሎ ፡ ቢታይም ፡ ትእዛዙ ፡ ራሱ ፡ ከሌሎች ፡ ትእዛዞች ፡ በተለየ ፡ መንገድ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በዝግጅቱ ፡ ውስጥ ፡ መካፈሉን ፡ አይገልጽም ። የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁ. ፩ ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጸድቆ ፡ የታወጀ ፡ መሆኑን ፡ ሲናገር ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጸድቆ ፡ የታወጀ ፡ መሆኑ ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። የአንቀጽ ፡ ፷፯ ፡ በትእዛዙ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ መጠቀስ ፡ የትእዛዙ ፡ አናቅጽት ፡ በምክር ፡ ቤቱ ፡ የተጻፉ ፡ መሆናቸውን ፡ ወይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ በጠቅላላው ፡ ትእዛዙንና ፡ የሕግ ፡ ክፍሉን ፡ ማስታወቂያ ፡ በማወጅ ፡ ረገድ ፡ ተካፋይ ፡ ስለሆኑ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ. ፷፯ ፡ ተሟልቷል ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ሊቀርቡ ፡ ይችላል ። ከነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ ክርክሮች ፡ አንደኛው ፡ እንኳን ፡ ተቀባይነት ፡ ቢያገኝ ፡ በጽሑፉ ፡ ቁ. ፷፯ ፡ አግባብ ፡ እንደሌለው ፡ ለማስረዳት ፡ የተሰጠው ፡ ክርክር ፡ ለቁ ፡ ፷፯ም ፡ አግባብ ፡ ይኖረዋል ።

የሚመለከተው ፡ አዋጅ ፡ በመጀመርያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ[9] ፡ በድንጋጌ ፡ መልክ ፡ አው ጥቶት ፡ ከዚያም ፡ ፓርላማው ፡ መክሮበት ፡ ጥቃቅን ፡ ለውጦች ፡ ካደረገበት ፡ በኋላ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አጽድቆት ፡ በአዋጅ ፡ መልክ ፡ ታወጀ ። በመንግሥት ፡ እየተመሩ ፡ ለትርፍ ፡ በሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ እንዲያቋቁሙ ፡ በግልጽ ፡ የሚፈቅድላቸው ፡ አንቀጽ ፡ በድንጋጌውም ፡ በአዋጁም ፡ ውስጥ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። እንግዲህ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይህንኑ ፡ አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አጽድቆታል ፡ ማለት ፡ ነው ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አዋጁን ፡ አጽድቆ ፡ ያወጀው ፡ ከትእዛዙና ፡ ከሕግ ፡ ማስታወቂያው[10] ፡ ወዲህ ፡ ስለሆነ ፡ አዋጁ ፡ ላንዳንድ ፡ የመን ግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ አግባብ ፡ እንዲኖረውና ፡ ከትእዛዙና ፡ ከሕግ ፡ ማስታወቂያ ውም ፡ ጋር ፡ በሚቃረንበት ፡ ጊዜ ፡ አዋጁ ፡ የበላይነት ፡ እንዲኖረው ፡ ወስኗል ፡ ማለት ፡ ነው ። ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ መወሰንና ፡ ማቀናበር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የግል ፡ ሥልጣን ፡ ቢሆንም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወጥቶ ፡ የንጉሠ ፡ ነገ ሥቱን ፡ ፍላጐት ፡ የሚያሳየው ፡ (አዋጁ) ፡ ከድሮዎቹ ፡ ሕግጋት ፡ ሁሉ ፡ ብልጫ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ።[11]

አዋጁና ፡ ትእዛዙ ፡ (በሥሩ ፡ ከወጣው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡) ጋር ፡ በሚጻረሩበት ፡ ጊዜ ፡ ትእዛዙ ፡ ብልጫ ፡ ይሰጠዋል ፡ ቢባልም ፡ እንኳን ፡ አሁን ፡

---

9. ድንጋጌ ፡ ቁ፡ ፺፬ ፤ ፲፱፻፶፬ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ፡ ፲፰ ።

10. የታወጀበት ፡ የጊዜ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ እንዲህ ፡ ነበር ፤ ትእዛዝ ፤ ድንጋጌ ፤ አሻሻይ ፡ ትእዛዝ ፤ የሕግ ፡ ማስታወቂያ ፤ አዋጅ ።
በማስታወሻ ፡ ቁጥሮች ፡ ፪ ፡ ፳ ፡ እና ፡ ፱ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥሮችና ፡ ቀኖች ፡ ተመልከት ።

11. እዚህ ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ የደረስነው ፡ በየትም ፡ የሚሠራበትን ፡ "በኋላ ፡ የወጡ ፡ ሕጐች ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ተቃራኒ ፡ ሕጐች ፡ ይሽራሉ ፡" የሚለውን ፡ ደምብ ፡ በመከተል ፡ ነው ። ኤች ፡ ቤካርት ፤ ኢንትሮዳክስዮን ፡ አሌቱድ ፡ ዱ ፡ ድሯ ፡ (፲፱፻፷፬) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፴፮-፪፻፴፯ ፤ ኤስ ፡ ኤድጋር ፡ ክሬይስ ፡ አን ፡ ስታትዩት ፡ ሎ ፡ (፯ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፷፫) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፫-፫፻፹፩ ፤ ሀልስበሪስ ፡ ሎውስ ፡ ኦቭ ፡ ኢንግለንድ ፡ (፫ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፰) ፡ ቮልዮም ፡ ፴፮ ፡ ስታትዩትስ ፡ ሴክሽን ፡ ፪፳፫ ፡ ፪፳፰ ፤ ኤም ፕላንዮል ፡ እና ፡ ገ ፡ ሪፔር ፤ ትሪትስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ (፲፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፴፱) ፡ (በሉዊዝያና ፡ ስቴት ፡ የሕግ ፡ ኢንስቲትዩት ፡ የተተረጐመ ፤ ፲፱፻፶፱) ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ክፍል ፡ ፩ ፡ ቁ. ፪፻፳፫ ፡ ፪፻፳፰ ፤ ቼቼ ኖቪች ፡ "በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አተረጓጐም ፤" የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ቮልዩም ፡ ፩ (፲፱፻፷፬) ፤ ገጽ ፡ ፫፻፳-፫፻፲፬ ፤ ዓለም ፡ አንተ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፤ ዘ ፡ ኢፌክት ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ፒናል ፡ ኰድ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ፕሪዝንስ ፡ ፕሮክላሜሽን ፡ ኦፍ ፡ 1944 ፡ ኤንድ ፡ ዘ ፡ ሪዛልቲንግ ፡ ስቴት ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ሎ ፡ (፲፱፻፷፰ ፡ ያልታተመ ፡ በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፡) ገጽ ፡ ፲-፲፰ ። በተ ጨማሪም ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ አተረጓጐም ፡ የሚናገር ፡ ደምብ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ መደምደሚያ ፡ ይደግፋል ። ይህም ፡ ደምብ ፡ "ሁለት ፡ አናቅጽት ፡ ግጭት ፡ የፈጠሩ ፡ እንደሆን ፡ አጠቃላይ ፡ ከሆነው ፡ አንቀጽ ፡ ይልቅ ፡ ነጣይ ፡ የሆነው ፡ ብልጫ ፡ ይሰጠዋል ፡" ይላል ። ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ኤድጋር ፡ ሃልስበሪ ፤ ፕላንዮልና ፡ ቼቼኖቪችን ፡ ተመልከት ። የአዋጁ ፡ አናቅጽት ፡ የሚናገሩት ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሠራተኞችና ፡ ሠራተኞቹም ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋምና ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ ስላላቸው ፡ መብት ፡ ሆኖ ፡ የትእዛዙና ፡ የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ አናቅጽት ፡ ደግሞ ፡ በጠቅላላው ፡ ስለመን ግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ እንጂ ፡ ነጠል ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ "ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡" ስለማይናገሩ ፡ የአዋጁ ፡ አናቅጽት ፡ ከትእዛዝና ፡ ከሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ብልጫ ፡ አላቸው ። ይህንን ፡ መደምደሚያ ፡ በመደገፍ ፡ በመጨረሻ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ ክርክር ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ የሚመለከተው ፡ የመንግሥቱን ፡ ውስጣዊ ፡ አቀዋምና ፡ የመንግሥቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ያላቸውን ፡ ግንኙነት ፡ መሆኑን ፡ ነው ። አበራ ፡ ጀምበሬ ፤ ዘ ፡ ፕሬሮጋቲቭ ፡ ኦቭ ፡ ዚ ፡ ኤምፐረር ፡ ቱ ፡ ዲተርምን ፡ ፓወርስ ፡ ኦቭ ፡ አድሚኒስትሬቲቭ ፡ ኤጀንሲስ ፡ (በዚሁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፭-፩፻፺፯ ፡ ይመለከቷል።) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለሕዝቡ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሰጡትን ፡ መብቶች ፡ (ማኅበር ፡ እንደማቋቋም ፡ ያሉትን ፡) ብቻውን ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ በጣም ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። ያሁኑ ፡ ሐተታ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወይም ፡ ፓርላማው ፡ በሕገ ፡ መንግ ሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፯ ፡ የተሰጠውን ፡ ማኅበር ፡ የማቋቋም ፡ መብት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ እስከምን ፡ ሊወስኑት ፡ ይችላሉ ፡ የሚለውን ፡ የተነሳሰረ ፡ ጥያቄ ፡ አይመለከትም ።

በምንከራከርበት ፡ ጭብጥ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መጻረር ፡ አናገኝም ። ከታች ፡ እን ደሚገለጸው ፡ ትእዛዙም ፡ ሆነ ፡ በሥሩ ፡ የወጣው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ እንዲያቋቁሙ ፡ በማንኛውም ፡ መንገድ ፡ አይከለክልም ።

እንግዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በተለይም ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ በመንግሥት ፡ እየተመሩ ፡ ለትርፍ ፡ የሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ (non - managerial) ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ እንዲያቋቁሙ ፡ ይፈቅድላቸዋል ። ይህንን ፡ የሚጻረር ፡ ሕግ ፡ የለም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ "የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ትእዛዝ ፡" እና ፡ በሥሩ ፡ የወጣው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ይህን ፡ የሚጻረር ፡ ሕግ ፡ ቢኖራቸው ፡ በቅርቡ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጸድቆ ፡ የታወጀው ፡ አዋጅ ፡ ብልጫ ፡ ስላለው ፡ ውድቅ ፡ ያደርጋቸዋል ።

ለ/ <u>የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በጠቅላላው ፤</u>

ሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ አይጠቃለሉም ። አር ሲ ሚንስ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በወጣ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ እንደጻፉት ፡ ሁሉ ፡ የነዚህና ፡ የሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በአዋጁ ፡ ውስጥ ፡ ያለመጠቃለል ፡ ውጤት ፡ ሠራተኞቹ ፡ በአዋጁ ፡ የተገለጸውን ፡ ዓይነት ፡ "ማኅበር ፡" ለማቋቋም ፡ ያለመቻላቸው ፡ ነው ።[12] አሠሪያቸው ፡ የሆነው ፡ መንግሥት ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ እንዲያደርግ ፡ የሚያስገድደው ፡ ሕግ ፡ የለም ። የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድም ፡ ከመንግሥት ፡ ጋር ፡ የሚገጥማቸውን ፡ ግጭት ፡ ለመመርመር ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ።[13]

አብዛኞዎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በአዋጁ ፡ ሥር ፡ ተጠቃለው ፡ ያለመገኘታቸው ፡ ብቻ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሌላ ፡ እንደ ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ያለ ፡ ማኅበር ፡ እንዳያቋቁሙ ፡ ተከልክለዋል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ይህ ፡ አዋጅ ፡ ሠራተኞች ፡ ፍላጐታቸውን ፡ ለማግኘት ፡ የሚያቋቁሙትን ፡ ማንኛውንም ፡ የማኅበር ፡ ዓይነት ፡ በሙሉ ፡ ለመቆጣጠር ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ እንዳንል ፡ ለዚህ ፡ ምንም ፡ መምሪያ ፡ የለንም ። ይልቁንም ፡ አዋጁ ፡ የሚናገረው ፡ ሥራ ፡ ለማቆምና ፡ ከአሠሪዎቻቸው ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ ስላላቸው ፡ "የሠራተኞች ፡ ማኅበር፡" ነው ። ከላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ አብዛኞዎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ የማቆምና ፡ ከአሠሪያቸው ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ ስምምነት ፡ የማድረግ ፡ መብት ፡ ስለሌላቸው ፡ አዋጁ፡ እነሱንም ፡ ያጠቃልላል ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ተገቢ ፡ አይሆንም ። እንግዲህ ፡ አዋጁን ፡ ያረቀቁት ፡ ሰዎች ፡ መደበኛ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሚያቋቁሙት ፡ ማኅበር ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ እንዲተዳደር ፡ አስበዋል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ አግባብ ፡ ባላቸው ፡ ሕግጋት ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ቅኝት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ 'የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡' የመሳሰሉ ፡ ማኅበሮችን ፡ እንዳያቋቁሙ ፡

---

12. "ሥራ ፡ ለማቋረጥ ፡ የማይችሉ ፡ ሠራተኞች ፡" የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፳ልዩም ፡ ፬ ፡ (፲፱፻፷፯) ገጽ ፡ ፻፷፰ ። ሚንስ ፡ እንደሚለው ፡ የሰጠው ፡ መደምደሚያ ፡ መደበኛ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በአዋጁ ፡ ውስጥ ፡ በተሰጠው ፡ ትርጉም ፡ መሠረት ፡ "ሠራተኞች ፡" አይደሉም ፡ የሚለውን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የተከተለ ፡ ነው ።

13. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፻፷፱ ፡ (የግርጌ ፡ ማስታወሻዎች ፡ አልተጠቀሱም) ።

በግልጽ ፡ የሚከለክላቸው ፡ ሕግ ፡ ያለመኖሩን ፡ ያሳያል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከላይ ፡ የጠቀስነው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ አንዳንድ ፡ አናቅጽት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ 'የሠራተኛ ፡ ማኅበርን ፡' በመሳሰሉ ፡ ድርጅቶች ፡ ተግባር ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ እንዳይሆኑ ፡ የበላዮቻቸው ፡ ሊከለክሏቸው ፡ ይችላሉ ፡ የሚሉ ፡ ቢመስሉም ፡ እነዚህን ፡ አንቀጾች ፡ በጥንቃቄ ፡ ከተመለከትናቸው ፡ የሕግ ፡ አውጪው፡ ሃሳብ ፡ ይኸ ፡ ያለመሆኑን ፡ ልንገነዘብ ፡ እንችላለን ።

ከታች ፡ እንደሚብራራው ፡ ለሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያው ፡ የምንሰጠው ፡ እንደዚህ ፡ዓይነቱ ፡ አተረጓጐም ፡ የሚደገፈው ፡ የሞያተኞችን ፡ ማኅበር ፡ በተለይ ፡ በሚጠብቀው ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍ ፡ ፵፯ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍ ፻፳፪ ፡ ውስጥ ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ፡" በሚለውም ፡ ሐረግ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በተከታታይ ፡ ያጸደቀችው ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ ስምምነት ፡ አግባብ ፡ ኖሮት ፡ ከላይ ፡ ለጠቀስነው ፡ ክርክር ፡ ድጋፍ ፡ ይሰጠዋል ።

ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በስተቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ አናቅጽት ፡ የሚገኙት ፡ በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ትእዛዝ ፡ ሥር ፡ በወጣው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፤ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ስለማኅበሮች ፡ ምዝገባ ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ በወጣው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ነው ።[14] የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍ ፡ ፹፩ ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ ይላል፡-

(፪) ማናቸውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚሰጠውን ፡ አገልግሎት ፡ የሚያጓድል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የተመደበበትን ፡ ሥራ ፡ የሚያጓድል ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ለተሰጠው ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ የውጭ ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ ክልክል ፡ ነው ።

(፫) ማናቸውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ካለበት ፡ ሚኒስቴር ፤ ቻርተር ፡ ካለው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ በጽሑፍ ፡ ሳይፈቅድለት ፡ ከተመደበበት ፡ ሥራ ፡ ውጪ ፡ ቢከፈለውም ፡ ባይከፈለውም ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ (ፕሮፌሽን) እንዳይሠራ ፡ ወይም ፡ ተካፋይ ፡ እንዳይሆን ፡ ክልክል ፡ ነው ። ሆኖም ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ የተቋቋሙ ፡ ማኅበሮች ፡ አባል ፡ ከመሆን ፡ የሚከለክለው ፡ ነገር ፡ የለም ።

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግና ፡ በሥሩ ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ በሌላ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ያልተጠቃለሉ ፡ "የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮችም" ፡ ጭምር ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እየተመዘገቡ ፡ እንዲቋቋሙ ፡ ይፈቅዳል [15] ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ከሕግ ፡ ውጪ ፡ ካልሆኑና ፡ ንጹሕ ፡ ሕሊናን ፡ የሚቃረኑ ፡ ካልሆኑ ፡

14. የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁ ፫፻፳፩ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፮ ።
15. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ፡ ፬፻፬ ፡ ፬፻፯ ፡ ፬፻፲፫ ፡ ፬፻፳፭ ፡ ፬፻፳፱ ፡ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ፡ ፲፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ "የማኅበሮች ፡ ምዝገባ ፡ ደምብ ፡" ቁ፡ ፬-፱ ።

በስተቀር ፡ ለመመዝገብ ፡ መብት ፡ አላቸው[16] ። ማንኛውም ፡ ማኅበር ፡ ሠራተኛው ፡ ለመንግሥቱ ፡ የሚሰጠውን ፡ ጥቅም ፡ ሳይነካ ፡ ወይም ፡ ከአገልግሎቱ ፡ ጋር ፡ ግጭት ፡ ሳይፈጥር ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከመንግሥት ፡ ሠራተኛነቱ ፡ ጋር ፡ ሳይጻረር ፡ ከንጹሕ ፡ ሕሊና ፡ ጋር ፡ ይቃረናል ፡ ብሎ ፡ ለመገመት ፡ ያዳግታል ። ስለዚህ ፡ ጥያቄው ፡ እንደ ዚህ ፡ ያሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ይጻረሩታል ፡ ተብሎ ፡ ክርክር ፡ ሊቀርብበት ፡ በሚችለው ፡ በትእዛዙ ፡ በቍጥር ፡ ፻፩(፪) ፡ እና(፫) ፡ መፍትሔ ፡ ሊያገኝ ፡ ይችል ፡ ይሆናል ።

እነዚህን ፡ አናቅጽት ፡ ለመመርመር ፡ በምንነሳበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ መልክ ፡ እንዳላቸው ፡ መገንዘብ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በአንድ ፡ በኩል ፡ አንዳንድ ፡ ተግባሮችን ፡ ሲከለክሉ ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ንዑስ ፡ ቍ. ፫ ፡ በኃይለ ፡ ቃል ፡ "የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በባለሞያዎች ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ እንዳይሆኑ ፡ ምንም ፡ አይከለክላቸውም ፡" [አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው] ፡ ይላል ። ነገሩን ፡ በግልጽ ፡ ለማስረዳት ፡ ሁለተኛውን ፡ መልክ ፡ በመጀመሪያ ፡ መመልከቱ ፡ ይጠቅመናል ።

የመጀመርያው ፡ ጥያቄ ፡ የሚመነጨው ፡ ከንዑስ ፡ ቁ (፫) ፡ የመጨረሻ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ነው ። መጀመርያ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሩ ፡ የሚለው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ "የሞያተኞች ፡ ማኅበር ፡" መደበኛ ፡ አባሎች ፡ ለመሆን ፡ ሲችሉ ፡ አለቆቻቸው ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ የመሪነቱን ፡ ቦታ ፡ በመውሰድ ፡ መልክ ፡ ተካፋይ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ፡ ነውን? ሁለተኛ ፡ "የሞያተኞች ፡ ማኅበሮች ፡" ምንድናቸው? ለነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ በምንሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ "ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ... ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ የሥራ ፡ ማኅበር ፡ ለማቆምና ፡ በማናቸውም ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ አለው ፡" [አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው]፡ በማለት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ ፴፯ ፡ የሚሰጠውን ፡ መብት ፡ ስፋት ፡ ማስታወስ ፡ ይኖርብናል ። በንዑስ ፡ ቁ (፫) ፡ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የመጨረሻው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ ፴፯ ፡ የተሰጣቸው ፡ መብት ፡ እንዳይታገድ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የተጨመረ ፡ አንክሮ ፡ ይመስላል ። ሕግ ፡ አውጪው ፡ ትእዛዙን ፡ ሲጽፍ ፡ በሃሳቡ ፡ ያለው ፡ ይኸ ፡ ባይሆንም ፡ እንኳን ፡ በግልጽ ፡ ጽፎ ፡ ካላሳየ ፡ በስተቀር ፡ የሚያወጣው ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ በግልጽ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሰጠውን ፡ መብት ፡ እንደወሰነ ፡ ወይም ፡ እንደከለከለ ፡ ተደርጎ ፡ መተርጎም ፡ የለበትም ። ከታች ፡ እንደ ምናየው ፡ የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚሰጠው ፡ ደንብ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፴፯ ፡ ጋር ፡ በማይጻረር ፡ መንገድ ፡ ሊነበብ ፡ (ሊተረጎም) ፡ ስለሚችል ፡ በሕገ ፡

16. የተጠየቁት ፡ ፎርማሊቲዎች ፡ እስከተሟሉ ፡ ድረስ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምዝገባ ፡ ሊከለከል ፡ ስለመቻሉ ፡ አይናገርም ። ይሁንና ፡ የማኅበሩ ፡ ዓላማዎች ፡ ሕግንና ፡ ንፁህ ፡ ሕሊናን ፡ የሚቃረኑ፡ ሆነው፡ ከተገኙ ፡ ማኅበሩን ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚገኘው ፡ የማኅበሮች ፡ ጽ/ቤት ፡ ሊሰርዘው ፡ ይችላል ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁ፡ ፬፻፸፪፡ የደንቡ ፡ አርቃቂዎች ፡ በብልሀነት ፡ እንዳጠቃለሉት ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ የተከለከሉ ፡ ዓላማዎች ፡ ያሏቸውን ፡ ማኅበሮች ፡ እንዳይ መዘግቡ ፡ ሊፈቅድላቸው ፡ ይገባል ። ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲመዘግብ ፡ ተገዶ ፡ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ እንዲሰርዝላቸው ፡ መጠየቅ ፡ ጊዜ ፡ ማባከን ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ደንቡ ፡ ሕግንና ፡ ንፁህ ፡ ሕሊናን ፡ የሚቃረኑ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዳይመዘገቡ ፡ ይላል ። ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁ፡ ፲፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም.የወጣው ፡ "የማኅበሮች ፡ ምዝገባ ፡ ደንብ ፡" ቁ፡ ፰(፩)(ለ) ። እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ በተጨማሪ ፡ "የታሰበው ፡ ማኅበር ፡ ዓላማ ፡ ብሔራዊ ፡ አንድነትን ፡ ወይም ፡ ጥቅምን ፡ የሚነካ ፡ ሲሆን ፡" የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ማኅበሩን ፡ እንዳይመዘግብ ፡ ይፈቅዳል ። ይህ ፡ ግልጽ ፡ ያልሆነ ፡ አንቀጽ ፡ በቁ፡ ፪(፩)(ለ) ፡ የሚጨምርበት ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ ቁ፡ ፬፻፸፱ ፡ ለአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ የሚተላለፍ ፡ ስለሆነ ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ። ኢሳይያስ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፤ ሊጋሊቲ ፡ አፍ ፡ ሎውስ ፡ ዲሊንግ ፡ ዊዝ ፡ አሶስዬሽንስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፤ (፲፱፻፷፰ በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፤ ያልታተመ) ፡ ገጽ ፡ ፹፩-፹፫ ፡ ይመለከቷል ።

መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፷፯ ፡ መሠረት ፡ የወጣ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሰጡትን ፡ መብቶች ፡ ለመወሰን ፡ ወይም ፡ ለመከል ከል ፡ ይችላል ፡ ወይ ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።

ከላይ ፡ የተጠየቀውን ፡ ጥያቄ ፡ የምንመልሰው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ለመመሥረት ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ቢሮ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያላቸውን ፡ ፍላጐት ፡ በበላዮቻቸው ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አድርገን ፡ መሆን ፡ የለበትም ። አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ በግልጽ ፡ ማኅበሮችን ፡ 'የማቋቋም' ፡ መብት ፡ መስጠቱ ፡ ብቻ ፡ ሳይ ሆን ፡ ሃገሪቱ ፡ ያለችበት ፡ የልማት ፡ ደረጃና ፡ መንግሥቱም ፡ በልማቱ ፡ በኩል ፡ በሚ ያከናውነው ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ምክንያት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ አባሎቻቸው ፡ የመንግ ሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሆኑ ፡ የሞያ ፡ ክፍሎች ፡ አሉ ። ለዚህም ፡ ምሳሌ ፡ የጋዜጠኝነት ፡ ሞያ ፡ ልንወስድ ፡ እንችላለን ። እነዚህ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ ሥልጣን ፡ ለመያዝ ፡ ያላቸው ፡ ችሎታ ፡ በአለቆቻቸው ፡ ፈቃድ ፡ እንዲገኝ ፡ መደረጉ ፡ የማኅበሮቹን ፡ መቋቋም ፡ ሊያጠፋው ፡ ባያጠፋውም ፡ ደግሞ ፡ የሚቋቋሙ ትን ፡ ማኅበሮች ፡ ቁጥር ፡ ሊቀንሰው ፡ ይችላል ። በተጨማሪም ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ሥልጣን ፡ ለመያዝ ፡ እጩ ፡ ለመሆን ፡ የማይችል ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሙሉ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይችልም ። እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ጠባብ ፡ አተረጓጐም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በነዚህ ፡ በማኅበሮች፡ ውስጥ ፡ ሙሉ ፡ አባል ፡ እንዳይሆኑ ፡ ስለሚያግ ዳቸው ፡ የንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ሦስትን ፡ የመጨረሻ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ዓላማ ፡ ያናጋዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አተረጓጐም ፡ በምክንያታዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ አይሆንም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ሦስት ፡ መጨረሻ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ "በሞያተኞች ፡ ማኅበሮች" ፡ ውስጥ ፡ ተራ ፡ ማኅበርተኛም ፡ የማኅበር ፡ ባለሥልጣንም ፡ እንዲሆኑ ፡ ይፈቅድላቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ።[17]

"የሞያተኞች ፡ማኅበር" ፡ ምንድነው? ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ በሁለት ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ሊከፈል ፡ ይችላል ። በመጀመርያ ፤ "የሞያተኞች ፡ ማኅበር" ፡ ማለት ፡ የአንድ ፡ በትምህርት ፡ የተገኘ ፡ እውቀት ፡ ሞያተኞች ፡ ማኅበር ፡ ማለት ፡ ነውን? ሁለተኛስ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ማኅበር ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ተግባሮች ፡ ሊያከናውን ፡ ይችላል? አባሎቹ ፡ የተሻለ ፡ ደሞዝና ፡ የተሻለ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲያገኙ ፤ የሚ ያስችላቸውን ፡ ተግባር ፡ ሊያከናውን ፡ ይችላልን? ለመጀመርያው ፡ ጥያቄ ፡ የሚሰ ጠው ፡ መልስ ፡ የአሉታ ፡ መሆን ፡ አለበት ። 'የሞያተኞች ፡ ማኅበር' ፡ በትምህርት ፡ እውቀት ፡ ያገኙ ፡ ሞያተኞችን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ተግባራቸው ፡ በዚሁ ፡ ሞያ ፡ የሚመ ራውን ፡ ሠራተኞችም ፡ ጭምር ፡ ማጠቃለል ፡ ይኖርበታል ። ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጥር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻ ፡ ዓ ም ፡[18] ካወጡት ፡ ሞያተኞች ፡ እንዳይሰደቡና ፡ ሰዳቢውም ፡ ቅጣት ፡ እንዲወሰንበት ፡ ከሚያዘው ፡ አዋጅ ፡ ወዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አንድ ፡ ሞያተኛ ፡ ከሌላው ፡ ሞያተኛ ፡ በታች ፡ አይደለም ፡ ለሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ብዙ ፡ መስዋእትነት ፡ አሳይቷል ። ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡

---

17. የንዑስ ፡ ቁ፡ (፫)ን ፡ የመጀመሪያ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ በሁለተኛው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ የተሰጡትን ፡ ተግ ባሮች ፡ እንኳን ፡ ለማከናወን ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የተሾሙባቸውን ፡ የበላይ ፡ የጽሑፍ ፡ ፈቃድ ፡ መጠየቅ ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ ለመተርጐም ፡ ይቻላል ። እንደነዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጥያቄ ፡ የማያስፈልግ ፡ የጽሕፈት ፡ ሥራ ፡ ስለሚጨምርና ፡ የሹሞቹንም ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚወስድ ፡ የመጀመሪያው ፡ አረ ፍተ ፡ ነገር ፡ የጽሑፍ ፡ ፈቃድ ፡ የሚጠይቀው ፡ በሁለተኛው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ላልተሰጡት ፡ ተግባ ሮች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ መተርጐም ፡ አለበት ።

18. ጀ ፡ ፓውል ፡ እና ፡ ሲ ፡ ክላፓም ፤ ኢትዮፒያን ፡ ኮንስቲትዩሽናል ፡ ዲቬሎፕመንት ፤ ኤ ፡ ሶውርስ ፡ ቡክ ፡ (፲፱፻፷፯) ፤ ገጽ ፡ ፫፻፱ ።

፴፰ ፡ ተጠብቆ ፡ ይገኛል ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ ፡ ፴፰ ፡ "በብሔራዊ ፡ (ሲቪል) ፡ መብቶች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደረግም" ፡ ይላል ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፴፪ ፡ ማኅበር ፡ ማቋቋምን ፡ በሠራተኞች ፡ በኩል ፡ ብሔራዊ ፡ መብት ፡ ያደርገዋል ። የሕግ ፡ ሞያተኞች ፡ ወይም ፡ ጋዜጠኞች ፡ ማኅበር ፡ እንዲያቋቁሙ ፡ ፈቃድ ፡ ሰጥቶ ፡ ተላላኪዎችን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የአንድ ፡ ሞያ ፡ አባሎችን ፡ ማኅበር ፡ እንዳያቋቁሙ ፡ መከልከል ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ን ፡ ከመጻረሩም ፡ ሌላ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፴፪ ፡ የተሰጠውን ፡ "ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ" ፡ የሚለውን ቅምግቢያ ፡ መሻር ፡ ይሆናል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፻፩(፫) ፡ በአንድ ፡ የተለየ ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ የተሰማሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ብቻ ፡ ማኅበር ፡ እንዲያቋቁሙ ፡ ይፈቅዳል ፡ ተብሎ ፡ መተርጐም ፡ አይገባውም ።

እንደዚህ ፡ ካልን ፡ ዘንድ ፡ የንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ሦስት ፡ መጨረሻ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር፡ የተመለከታቸው ፡ የማኅበር ፡ ዓይነቶች ፡ ምንድናቸው? ፡ ከሥራቸው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡የጋራ ፡ ፍላጐታቸው ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ሰዎች ፡ ማኅበሮች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።[19] በመላው ፡ ዓለም ፡ የእንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ዓላማ ፡ የጋራ ፡ ጥቅምን ፡ በሚነኩ ፡ ጥያቄዎች ፡ ላይ ፡ መወያየት ፤ ሞያቸውን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ማራመድና ፡ ማኅበርተኞች ፡ በሞያው ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ፍላጐትና ፡ ስሜት ፡ ማስፋፋት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ማኅበሮች ፡ በማንኛውም ፡ አገር ፡ ሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ በመሻት ፡ የማኅበርተኞቻቸውን ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ በሕብረት ፡ ይጥራሉ ። ይህንን ፡ ፍሬ ፡ ነገርና ፡ "ለማንኛውም ፡ የሥራ ፡ ዓይነት ፡ ለተሠማሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡" የተሰጠውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ጥበቃ ፡ እየተመለከትን ፡ በሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ "የሞያተኞች ፡ ማኅበር" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ጥቂት ፡ የሞያ ፡ ክፍሎችን ፡ የሚያጠቃልል ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አስቸጋሪ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጠባብ ፡ አተረጓጐም ፡ ተቀባይነት ፡ የሚኖረው ፡ ይኸው ፡ አተረጓጐም ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ ተፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡አግባብ ፡ ያላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋት ፡ የቁጥር ፡ ፻፩ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥሮች ፡ (፪) ፡ እና ፡ (፫) ፡ ናቸው ። ማንኛውም ፡ ሠራተኛ ፡ የሚሠራበትን ፡ ሁኔታ ፡ የማሻሻል ፡ ፍላጐት ፡ ስላለው ፡ ለአንድ ፡ ድርጅት ፡ ላለው ፡ አባልነት ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣንነት ፡ የሚያደርገው ፡ መስዋእትነት ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ቢገፋም ፡ እንኳን ፡ በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ መካከል ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ከታወቀው ፡ ግጭት ፡ የበለጠ ፡ ግጭት ፡ ሊፈጠር ፡ አይችልም ። የተቀጠረበትን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ በሚገባው ፡ ጊዜ ፡ የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ እስከሚሠራ ፡ ድረስ ፡ ቁጥር ፡ ፻፩ንም ፡ ሆነ ፡ ሌላውን ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ቁጥር ፡ አይተላለፍም ። በሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ሌላ ፡ ሕጐች ፡ ለመጣስ ፡ የሚችሉ ፡ የማኅበሩ ፡ ተግባሮች ፡ ሥራ ፡ ማቆምና ፡ ለሥራ ፡ እምቢተኝነትን ፡ የሚያተርፉ ፡ ስምምነቶች ፡ ናቸው ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ተግባሮች ፡ በቁጥር ፡ ፻፫ ፡ በግልጽ ፡ ተከልክለዋል ።[20] ማኅበሩ ፡ በቁጥር ፡ ፻፫ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ወሰኖች ፡ አውቆ ፡ እስከ ፡ ተቀበለ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ከዓላማዎቹ ፡

19. በሥራቸው ፡ ላይ ፡ በተመሠረተ ፡ የጋራ ፡ ጥቅማቸውን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ማኅበር ፡ ማቋቋም ፡ እንደሚችሉ ፡ የተደረገው ፡ ወሰን ፡ በሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ "የሞያተኞች ፡ ማኅበር ፡" በሚለውና ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ ባንድ ፡ መስክ ፡ የተሰማሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ በሚለው ፡ የተፈለገ ፡ ይመስላል ።

20. በጠቅላላው ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ሚንስን ፡ ይመለከቷል ። ሚንስ ፡ እንደሚያሳየው ፡ ሁሉ ፡ እንኳን ፡ አዋጁ ፡ በመንግሥት ፡ እየተመሩ ፡ በሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ ለሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ አግባብ ፡ እስካለው ፡ ድረስ ፡ እነዚህን ፡ አናቅጽቶች ፡ ይሸራቸዋል ።

መካከል ፡ የማኅበርተኞችን ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ የሚጥር ፡ ማኅበር ፡ ለማቋ ቋምና ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ የማይችሉበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

ይህ ፡ አተረጓጐም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ያለመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ አላፊ ፡ ወይም ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፈቃድ ፡ በሞያ ፡ ተግባሮች ፡ ተካፋይ ፡ እዳይሆኑ ፡ የሚከለክ ለውን ፡ የቁ ፹፩(፫)ን ፡ የመጀመሪያ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ያደርገዋል ፡ የሚል ፡ መቃወሚያ ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ መቃወሚያ ፡ ቀዋሚ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ ምክንያቱም ፡ አተረጓጐሙ ፡ ከሞያተኞች ፡ ማኅበሮች ፡ ጋር ፡ የተያያዙትን ፡ ተግባ ሮች ፡ በመጀመርያው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ከተሰጡት ፡ "ሞያ ፡ ነክ ፡ ተግባ ሮች ፡" ሁለተኛው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ የመጀመርያው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ማኅበር ፡ ነክ ፡ የሆኑትን ፡ ጉዳዮች ፡ እንዲመለከት ፡ ባለመታሰብ ፡ ስለሚያገባቸው ፡ ነው ። የመጀመ ርያው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ አሁንም ፡ ሞያ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ተግባሮችን ፡ እንዳያከናውኑ ፡ ይከለክላል ። ለምሳሌ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሆኑ ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ልግል ፡ ደምበኞቻቸው ፡ ያለ ፡ አለቆቻቸው ፡ ፈቃድ ፡ እንዳይከራከሩ ፡ ይከለክላል ።

ሌላው ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ መቃወሚያ ፡ ደግሞ ፤ ሥራ ፡ ለማቆም ፡ የማይ ችል ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ዋጋ ፡ ስለሌለው ፡ ትእዛዙም ፡ ሆነ ፡ የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲቋቋሙ ፡ ይፈቅዳሉ ፡ ተብለው ፡ መተርጐም ፡ የለባቸውም ፡ የሚል ፡ ነው ። ይሁንና ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ማኅበር ፡ ለማኅበርተኞችም ፡ ሆነ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ጥቅም ፡ ሊያስገኝ ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ ቁጥራቸው ፡ በዛ ፡ ያለ ፡ ሰዎች ፡ በመሰብሰብ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ መሠ ረት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አቤቱታ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ቢያደርግ ፡ አቤቱታውን ፡ አሳ ሳቢ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ። በተጨማሪም ፡ ዜና ፡ ሰብሳቢ ፡ አካል ፡ አደራጅቶ ፡ ዜናዎችን ፡ በመሰብሰብ ፡ በአባሎቹ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መበላለጥ ፡ ተገንዝቦ ፡ ይህንኑ ፡ ለማሻሻል ፡ የሥራ ፡ ኃይሉን ፡ በየአስፈላጊው ፡ አቅጣጫ ፡ ሊዘ ረጋ ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ዜና ፡ ለሱፐርቫይዘሮችና ፡ ለመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በማቀበል ፡ የመንግሥቱን ፡ ሠራተኞች ፡ አገ ልግሎት ፡ ሊያሻሽለው ፡ ይችላል ።

የሕጉ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ መተርጐም ፡ ማኅበር ፡ የማቋቋምን ፡ ነፃነት ፡ የሚመ ለከተውንና ፡ መብቱንም ፡ ለመጠበቅ ፡ የተደረገውን ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ስምምነት ፡ ቁ. ፹፯ን ፡ ይደግፋል ። ከዚያም ፡ አልፎ ፡ ተፈላጊ ፡ ነው[21] ። ኢትዮጵያ ፡ ይህንን ፡ ስምምነት ፡ ማጽደቋ ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ግንቦት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተመዝግቧል ።[22] እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዚህ ፡ ስምምነት ፡ ተካፋይ ፡ ነች ። ስለሆነችም ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ይኸው ፡ ስምምነት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ "የበላይ ፡ ሕጐች" ፡ ውስጥ ፡ ይቆጠራል ። እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ስምምነት ፡ ጋር ፡ የሚጻረር፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ይሆናል ። የሕግ ፡ ክፍሉ ፡ ማስታወቂ ያም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበርን ፡ የመሳሰሉ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዳያቋቁሙ ፡ ወይም ፡ አባል ፡ እንዳይሆኑ ፡ ከልክሏቸዋል ፡

---

21. ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኞች ፡ ድርጅት ፤ ኮንቬንሽንስ ፡ ኤንድ ፡ ሪኮሜንዴሽንስ ፡ (፲፱፻፷፮) ፤ ገጽ ፡ ፰፻፷፫-፰፷፯ ።

22. አማኑኤል ፡ ነጋሣ ፤ ፀ ፡ ኢምፓክት ፡ ኦፍ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሌበር ፡ ስታንዳርድስ ፡ ኦን ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሌበር ፡ ሌጅስሌሽን ፤ (፲፱፻፷፱ ፡ በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፤ (ያልታተመ ፡) ገጽ ፡ ፺፪ ።

በመባል ፡ ተተርጉሞ ፡ ቢሆንም ፡ ኖሮ ፡ እነዚያ ፡ ሕጐች ፡ አዲስ ፡ በተወረሰው ፡ "የበላይ ፡ ሕግ" ፡ መሻሻል ፡ ይኖርባቸዋል ። ይህም ፡ መደምደሚያ ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ንግግር ፡ የተከተለ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ ስምምነት ፡ ቁ. ፹፯ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበርን ፡ የመሳሰሉ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲያቋቁሙ ፡ ከፈቀደ ፡ ሌሎች ፡ ሕጐች ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዳይቋቋሙ ፡ ይከለክላሉ ፡ ተብለው ፡ መተርጐም ፡ የለባቸውም ። እነዚህ ፡ ሕጐች ፡ በቅድምያ ፡ ያላቸው ፡ ትርጉም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበርን ፡ የመሳሰሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ለማቋቋም ፡ አይችሉም ፡ የሚል ፡ ከሆነም ፡ የዓለም ፡ አቀፉ ፡ ስምምነት ፡ በተከታታይነት ፡ መጽደቁ ፡ ሊያሻሽላቸው ፡ ይገባል ። ካልሆነ ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሕጐች ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ።

የዓለም ፡ አቀፉ ፡ ስምምነት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "ሠራተኞች ፡ --- ምንም ፡ ዓይነት ፡ ልዩነት ፡ ሳይፈጠርባቸው ፡ --- በቅድሚያ ፡ ፈቃድ ፡ መጠየቅ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ --- የመረጡትን ፡ ድርጅት ፡ ለማቋቋምና ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ አላቸው ።"[23]

'ድርጅት' ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ "ሠራተኞች ፡ ፍላጐታቸውን ፡ ለማስከበር ፡ --- የሚያቋቁሙት ፡ ማንኛውም ፡ ድርጅት ፡ ---"[24] በመባል ፡ ተተርጉሟል ። በተጨማሪም ፡ ይኸው ፡ ስምምነት ፡ እነዚህ ፡ ድርጅቶች ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ሳይኖርባቸው ፡ የሥራ ፡ መምሪያቸውን ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ ይፈቅዳል ።[25] የዚሁ ፡ ስምምነት ፡ ቁጥር ፡ ፰ም ፡ "ሠራተኞች ፡ አሠሪዎችና ፡ ድርጅቶቻቸው ፡ በዚህ ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ በተሰጣቸው ፡ መብት ፡ በሚጠቀሙበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችና ፡ ድርጅቶች ፡ የሀገራቸውን ፡ ሕግ ፡ ማክበር ፡ ይኖርባቸዋል ።" ይልና ፡ ቀጠል ፡ በማድረግ ፡ "የሀገራቸው ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ስምምነት ፡ የተሰጣቸውን ፡ ዋስትና ፡ መጉዳት ፡ ወይም ፡ እንደሚጐዳ ፡ ሆኖ ፡ መፈጸም ፡ የለበትም ፡" ይላል ።[26]

እንግዲህ ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ ስምምነት ፡ ቁጥር ፡ ፹፯ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የበላይ ፡ ሕጐች ፡ አንዱ ፡ በመሆኑ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የመንግሥትና ፡(የፖሊስ ፡ ሠራዊትና ፡ የጦር ፡ ኃይሎች ፡ በስምምነቱ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ መሠረት ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ አይጠቃለሉም) ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ፍላጐታቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ማኅበር ፡ የማቋቋም ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ ይሰጣቸዋል ።

---

23. ቁጥር ፡ ፪ ።

24. ቁጥር ፡ ፲ ።

25. ቁጥር ፡ ፫ ።

26. ኢንተርናሽናል ፡ ሌበር ፡ ኦፊስ ፤ ዘ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሌበር ፡ ኮድ ፤ (፲፱፻፶፩) ፤ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፤ ፯፻፹፩ ፡ ቁ፡ ፫ ፡ ማኅበር ፡ የማቋቋምና ፡ የጋራ ፡ ስምምነት ፡ ማድረግ ፡ ተከታታይ ፡ መብቶች ፡ ስምምነት ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ኮንቬንሽን ፡ ቁ፡ ፺፰ ፤ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችን ፡ በግልጽ ፡ ከሚሰጠው ፡ መብት ፡ ይነጥላቸዋል ። እነዚህ ፡ መብቶች ፡ የጋራ ፡ ስምምነትን ፡ ያጠቃልላሉ ። ቁ፡ ፮ ፡ ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፯፻፺፯ ። ይሁንና ፡ የብቁው ፡ ደርግ ፡ ማብራርያ ፡ ሪፖርት ፡ ደርጉና ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ሌበር ፡ ኦፊስ ፡ ሕግ ፡ አማካሪዎች ፡ ኮንቬንሽን ፡ ቁ፡ ፹፯ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችን ፡ ያጠቃልላል ፡ ብለው ፡ መገመታቸውን ፡ ይገልጻል ። ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፯፻፺፯-፯፻፺፩ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ፡ ፳፫ ። ሥዩም ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘ ፡ ዲቬሎፕመንት ፡ ኦቭ ፡ ሳም ፡ ኢንስቲትዩሽንስ ፡ ኮንሰርንድ ፡ ዊዝ ፡ ሌበር ፡ ሪሌሽንስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፤ (፲፱፻፷፱ ፡ የተባዛ ፤ የመንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ) ፡ ገጽ ፡ ፻፱-፻፫ ፡ በተጨማሪ ፡ ይመለከቷል ። (አቶ ፡ ፍስሐ ፡ ጽዮን ፡ ተኪኤ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ኰንፌደሬሽን ፡ ጸሐፊ ፡ በባለ ፡ ሦስት ፡ ክፍሉ ፡ ብሔራዊ ፡ ኢንዱስትሪያል ፡ ግኑኙነት ፡ እ. ኤ. አ. ኦገስት ፡ ፳፫-፳፯ ፡ በተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ በአፍሪካ ፡ አደራሽ ፤ ያደረጉትን ፡ ንግግር ፡ በመጥቀስ ። )

ይህ ፡ መብት ፡ የተነፈጋቸው ፡ ሰዎች ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ መሠረት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብና ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ እና ፡ ፻፲ ፡ መሠረት ፡ ክሳቸውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማሰማት ፡ ከመቻላቸውም ፡ በላይ ፡ በሠራተኞች ፡ ስብሰባ ፡ በኩል ፡ በደላቸውን ፡ ለዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላሉ ።[27] የዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ አንድ ፡ አባል ፡ መንግሥት ፡ ያጸደቀውን ፡ ስምምነት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አላዋለም ፡ ብሎ ፡ ከወሰነ ፡ ስምምነቱ ፡ በዚሁ ፡ መንግሥት ፡ ተቀባይነትና ፡ ዋጋ ፡ እንዲኖረው ፡ ለማድረግ ፡ መሞከር ፡ ይችላል [28] ።

## <u>መደምደሚያ ፤</u>

የኢትዮጵያን ፡ መደበኛ ፡ ሕጐች ፡ ለብቻቸው ፡ እንዲሁም ፡ እነዚሁኑ ፡ ሕጐች ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ 'የበላይ ፡ ሕግ' ፡ ከሚለው ፡ ሐረግና ፡ ከዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ ስምምነት ፡ ቁጥር ፡ ፹፯ ፡ ጋር ፡ በማጣመር ፡ የተደረገው ፡ ጥናት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበርን ፡ የመሰሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ለማቋቋም ፡ መቻላቸውን ፡ ያሳያል ። በመንግሥት ፡ እየተመሩ ፡ ለትርፍ ፡ በሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ ለሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ይኸው ፡ መብትና ፡ በመብቱም ፡ የመጠቀሚያው ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ተሰጥተዋል ። እነዚህ ፡ ሠራተኞች ፡ የአዋጁን ፡ አናቅጽት ፡ በመከተል ፡ የሚያቋቁሚቸውን ፡ ማኅበሮች ፡ የሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገትና ፡ ማኅበራዊ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ እንዲመዘግብላቸው ፡ መብት ፡ ተሰጥቷቸዋል ። ሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችም ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበርን ፡ የመሳሰሉ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዳያቋቁሙ ፡ አልተከለከሉም ። እንዲያውም ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ ስምምነት ፡ ቁጥር ፡ ፹፯ ፡ ከፖሊሶችና ፡ ከጦር ፡ ኃይሎች ፡ በስተቀር ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ማኅበር ፡ እንዲያቋቁሙ ፡ ይፈቅዳል ። እነዚህ ፡ ሠራተኞች ፡ የሚያቋቁሙትን ፡ ማኅበር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በማስመዝገብ ፡ በመብታቸው ፡ ሊጠቀሙ ፡ ይችላሉ ። ይሁንና ፡ በመንግሥት ፡ እየተመሩ ፡ ለትርፍ ፡ በሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ እንደሚሠሩት ፡ ሠራተኞች ፡ ሌሎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ አሠሪያቸውን ፡ ማለትም ፡ መንግሥትን ፡ ከማኅበራቸው ፡ ጋር ፡ የጋራ ፡ ስምምነት ፡ እንዲያደርግ ፡ ሊያስገድዱት ፡ አይችሉም ። እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ድጋፋቸውን ፡ በመንግሥቱ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ሃላፊነት ፡ ባለባቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መልካም ፡ አሳቢነት ፡ ወይም ፡ ማኅበራቸው ፡ የያዘውን ፡ አቅዋም ፡ መንግሥቱ ፡ በጥብቅ ፡ እንዲመረምረው ፡ ሊገፋፉ ፡ በሚችለው ፡ በብሩሑ ፡ ሕዝባዊ ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ መፈለግ ፡ አለባቸው ።

---

27. ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ <u>ስምምነት</u> ፡ (የ1955 እትም) ፡ አንቀጽ ፡ 24 ። ኢትዮጵያ ፡ የድርጅቱ ፡ አባል ፡ የሆነችው ፡ የቀድሞው ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ በሆነችበት ፡ በ1923 ፡ (እ. ኤ. አ.) ነው ። አማኑኤል ፡ ነጋሣ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ 22 ፡ የተጠቀሰ ፤ ገጽ ፡ 8—10 ፡
28. ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ <u>ስምምነት</u> ፤ አንቀጽ ፡ 25—34 ።